የወ/መ/ቁጥር 159716

የልደታ ምድብ 1 ኛ ወንጀል ችሎት

ሐምሌ 21 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፡ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ አያና አበበ ቀረበ

ተከሳሽ፡ አቶ ባደግ ውጅራ ሰማን - ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ህዳር 08 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ ተከሳሽ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 669(2)(መ) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ የማይገባውን ብልፅግና ለራሱና ለሌላም ለማስገኘት አቅድ ቀኑና ወሩ ባልታወቀበት በ2002 ዓ.ም በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 07/14 ክልል ልዩ ቦታው ሰንጋተራ እየተባለ ከሚጠራው አካባቢ በግል ተበዳይ አቶ ለገሠ ደምሴ የምግብና የመጠጥ ግሮሰሪ ውስጥ በመስተንግዶ ስራ ላይ ተቀጥሮ በመስራት ላይ እንዳለ የቀን ሂሳብ የሚቀመጥበትን የብረት ካዝና ቁልፍ ከግል ተበዳይ ላይ ሰርቆ በመውሰድ በሶስት ከፒ ካስቀረፀ በኋላ አማኑ ውጅራ ለተባለውና በግል ተበዳይ የንግድ ቤት ውስጥ በብርጭቆ አጣቢነት ተቀጥሮ ለሚሰራው ታናሽ ወንድሙ በመስጠት ከግል ተበዳይ ላይ ብር ሰርቆ እያመጣ እንዲሰጠው ነግሮት አማኑ ውጅራ የተባለው ግምቱ 9,960.00(ዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ብር) የሚሆን ገንዘብ በተለያዩ ቀኖች በመስረቅ ለተከሳሹ ወስዶ የሰጠ ሲሆን በድጋሚ ጥቅምት 21 ቀን 2002 ዓ.ም ከሌሊቱ በግምት 6፡15 ሰዓት ሲሆን የብር ማስቀመጫ ከዝናውን በመክፈት ብር 750.00(ሰባት መቶ ሃምሳ ብር) ሲሰርቅ እጅ ከፍንጅ በመያዙ ተከሳሹ ወንጀሉ የሚፈፀምበትን የካዝና ቁልፍ ከማቀበል ጀምሮ የወንጀል ድርጊቱን ፍሬ ተቀበሎ በመገልገል በወንጀል ውጤቱ ሙሉ በሙሉ ተካፋይ በመሆኑ በፈፀመው ከባድ የስርቆት ወንጀል ተከሷል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ደርሶትና ተነቦለት ከተረዳው በኋላ ክሱን ሳይቃወም፤ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም ብሎ ክዶ በመከራከሩ ዐ/ሕግ የግል ተበዳይን ጨምሮ አራት ምስክሮችን በማቅረብ ያሰማ ሲሆን የግል ተበዳይ ተከሳሽን በሰራተኝነት ቀጥሮ ያሰራው እንደነበር፤ ከዚያም እሱ ከለቀቀ በኋላ ታናሽ ወንድሙ አማኑ ውጅራ የተባለው ገብቶ በመስራት ላይ እያለ በተለያየ ጊዜ ገንዘብ እየሰረቀ ይወስድ እንደነበር፤ ከዚያም ጥቅምት 21 ቀን 2002 ዓ.ም ሌሊት 6፡15 ሰዓት የተከሳሽ ታናሽ ወንድም የሆነው ከግል ተበዳይ ንግድ ቤት የገንዘብ ማስቀመጫ ውስጥ

ገንዘብ ሲያወጣ መያዙን፤ የያዙትም ከግል ተበዳይ ጋር ቀርበው የመሰከሩት ሁለተኛ እና ሦስተኛ ምስክሮች ናቸው። አራተኛ ምስክር ደግሞ ተከሳሽ በወቅቱ ፖሊስ ጣቢያ ሆኖ በነፃ ፍቃዱ ድርጊቱን በታናሽ ወንድሙ በኩል እንዴት እንዳስፈፀመ አስረድቷል። ከዚህ ሌላ ተከሳሽ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 27(2) መሰረት በሰጠው ቃል ድርጊቱን ተከሳሽ በታናሽ ወንድሙ አማኑ ውጅራ በተባለው አማካኝነት እንዴት እንደፈፀመው ማለትም ተከሳሽ የግል ተበዳይ ሰራተኛ እያለ የገንዘብ ማስቀመጫ ቁልፉን በማስቀረፅ ለታናሽ ወንድሙ በመስጠት በየዕለቱ ብር 100.00(አንድ መቶ ብር) ብቻ በመስረቅ በክሱ ላይ የተገለፀውን ገንዘብ ያህል እንዲሰረቅ ስለማድረጉ አምኖ ቃሉን ሰጥቷል። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተከሳሽ በክሱ ላይ የተገለፀውን የስርቆት ድርጊት እቅዱን ከማውጣት ጀምሮ የውጤቱ ተካፋይ እስከ መሆን ድረስ የድርጊቱ ተካፋይ መሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ ተከሳሽ በተከሰሰበት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 669(2)(መ) ስር እንዲከላከል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዟል።

ተከሳሽም እከላከላለሁ ብሎ ሁለት የመከላከያ ምስክሮችን በማቅረብ ያሰማ ሲሆን በመከላከያ ጭብጥነትም የወንጀል ድርጊቱን አለመፈፀሜን አስረዳለሁ፤ ምክንያቱም ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት ጊዜ በቦታው አልነበርኩም፤ በፖሊስ ጣቢያም ቃሌን አልሰጠሁም፤ አልፈርምኩም፤ የግል ተበዳይ የተባለውን አቶ ለገሠ ደምሴንም አላውቀውም፤ ታናሽ ወንድሜ ከግል ተበዳይ ጋር ስለመስራቱም አላውቅም፤ የመከላከያ ምስክሮቼ ድርጊቱን ያለመፈፀሜን ያስረዳሉ፤ ምክንያቱም ሁለቱም ምስክሮቼ ከእኔ ጋር አንድ ላይ ነው የምንሰራው፤ ይሄውም ስታድዮም አካባቢ ከሚገኘው ጌታ ዘሩ ሥጋ ቤት ከመስከረም 2002 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 2002 የሁዳዴ ፆም መግቢያ ድረስ አብረን እየሰራን ነበር የሚለውን አስመዝግቦ ሁለቱ ምስክሮችም ቀርበው መኃላ ፈፅመው የመሰከሩ ሲሆን ቃላቸውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል።

ፍ/ቤቱም ተከሳሽ ባቀረባቸው ሁለት የመከላከያ ምስክሮች ቃል በዐ/ሕግ በኩል የቀረበበትን ክስና ማስረጃ አስተባብሏል ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን ሁለቱ የተከሳሽ የመከላከያ ምስክሮች የሰጡት ቃልና ተከሳሽ ያስመዘገበው ጭብጥ እርስ በእርሱ የሚጋጭና የተለያየ ነው። ተከሳሽ እስከ የካቲት ወር 2002 ዓ.ም የአብይ ፆም መግቢያ ድረስ ጌታዘሩ ከተባለው ሥጋ ቤት ከመከላከያ ምስክሮቹ ጋር አብረን እንሰራ ነበር በማለት ቃሉን ሲያስመዘግብ፤ አንደኛው የመከላከያ ምስክር በሰጠው ቃል ግን እስከ አሁን ድረስ(የምስክርነት ቃል የተሰጠበት ግንቦት 25 ቀን 2002 ዓ.ም) አብረን እየሰራን ነው፤ የምንሰራውም በፊት ከምንሰራበት ሥጋ ቤት ነው፤ ጌታዘሩ ሥጋ ቤት ግን አብረን ሰርተን አናውቅም በማለት አስረድቷል። ሁለተኛው የመከላከያ ምስክርም ከተከሳሽ

ጋር አብረው ስታድዮም አካባቢ ካለው ሥጋ ቤት አብረው እንደሚሰሩ እንደነበር፤ አሁን ግን ወጥተው ሌላ እዚያው አካባቢ ሥጋ ቤት አብረው እንደሚሰሩ አስረድቷል። የመከላከያ ምስክሮቹ ቃልና የተከሳሽ ጭብጥ አንድነት የሌለው ሲሆን ቢኖረው ኖሮ እንኳ ተከሳሽ ታናሽ ወንድሙ

የሆነውን አማኑ ውጅራን ከግል ተበዳይ የንግድ ቤት ተቀጥሮ ሲሰራ በየጊዜው ገንዘብ እየሰረቀ በተለያየ ጊዜ ከብር 9,000.00(ዘጠኝ ሺህ ብር) በላይ ተሰርቆ እንዲሰጠው አድርጓል ተብሎ የቀረበበትን ክስና ማስረጃ የሚያስተባብል ሆኖ አልተገኘም። በፖሊስ ጣቢያ ምስክር ባለበት የወንጀል ድርጊቱን እንዴት እንደፈፀመ ያስረዳበትን ሁኔታ የሚያስተባብል ማስረጃም አላቀረበም። ይሁን እንጅ ከመከላከያ ምስክሮቹም ሆነ ቀደም ሲል በዐ/ሕግ በኩል ቀርብ ከተሰሙት ምስክሮች ቃል ፍ/ቤቱ ለመገንዘብ እንደቻለው የወንጀል ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት ወቅት ተከሳሽ የግል ተበዳዩ ሰራተኛ ሳይሆን በሌላ ቦታ እየሰራ እንደነበር የተረጋገጠ ስለሆነ፤ ድርጊቱንም የፈፀመው በታናሽ ወንድሙ አማኑ ውጅራ በተባለውና በወቅቱ የግል ተበዳይ ሰራተኛ በሆነው ግለሰብ በኩል ስለሆነ፤ ተከሳሽ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 669(2)(መ) ስር ሳይሆን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 665(1) ስር ጥፋተኛ ነው በማለት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 113(2) እና 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ በተከሳሽ ላይ የምናቀርበው የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የለም፤ ፍ/ቤቱ ተከሳሽን የሚያርምና የሚያስተምር ቅጣት ይወስን በማለት አመለከተ።

<u>ተከሳሽ</u>፡ ዕድሜዬ 17 ዓመት ነው፤ የትምህርት ደረጃዬ 8 ኛ ክፍል ነው፤ በለውዝ መሸጥ ሥራ ነው የምተዳደረው፤ በዚህ ወንጀል ፖሊስ ጣቢያ 24 ቀን ታስሬያለሁ በማለት አመለከተ።

ፍ/ቤቱም መዝገቡን መርምሮ የሚከተለው የቅጣት ውሳኔ ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ሊያሳካ እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወስነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ከብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ

የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሽ አሁን ጥፋተኛ የተባጀበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 665(1) ደረጃ የወጣለት ወንጀል በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል አንድ እና አባሪ 3 መሰረት የተመለከተው ደረጃ 4 ሲሆን ተጓዳኝ መነሻ እርከኑም 8 ነው። ስለሆነም የዚህ እርከን መነሻ ፈቃደ ስልጣን/range/ ከአንድ ዓመት ከሁለት ወር እስከ አንድ ዓመት ከስምንት ወር እስራት የሚያስቀጣ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም ፍ/ቤቱ ቅጣቱን የሚወስነው የተከሳሽን የትምህርት ደረጃና ዕድሜ ከግምት ውስጥ በማስገባት መነሻ ቅጣቱ አንድ ዓመት ከሦስት ወር ቀላል እስራት እንዲሆን ነው ያደረገው።

በዚህም መሰረት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ቅጣት ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84 ወይም 85 መሰረት የቅጣት ማክበጃ፤ ተከሳሽም በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 እና 86 መሰረት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ያላቀረቡ ስለሆነ ፍ/ቤቱ የመነሻውን ቅጣት እርከኑን ከፍም ሆን ዝቅ ሳያደርግ እንዳለ እርከን 8 ን ወስዶታል። በመሆኑም በዚሁ እርከን 8 መሰረት የተወሰነው የአንድ ዓመት ከሦስት ወር ቀላል እስራት ተከሳሽ እንዲቀጣ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. በተከሳሽ ላይ የተወሰነውን የአንድ ዓመት ከሦስት ወር ቀላል እስራት የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ከዛሬ ጀምሮ በማሰብ እንዲያስፈፅም ታዟል። ማ/ቤት ተከሳሽ በፖሊስ ጣቢያ 24 ቀናት የታሰረበትን በቅጣቱ ታሳቢ እንዲያደርግ ታዟል።ይፃፍ።

2 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

3 ኛ. በዚህ መዝገብ የተሰጠ የዋስትና ግዴታ ካለ ቀሪ ሆኗል።

4 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።